# የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር ሙያዊ የስነ-ምግባር፣ የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ ቁጥር 161/2016

Teachers and School Leadership Professional Ethics, Disciplinary Procedures and Complaints Procedures (Directive No. 161/2016)


የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
Addis Ababa City Administration Education Bureau



ነሐሴ 1፥ 2016

የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር

ሙያዊ የስነ-ምግባር፣የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ

ትምህርት የዕድገት ሁሉ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ ለሁለንተናዊ ልማት መፋጠን ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ትምህርት ተመራማሪና ችግር ፈቺ ዜጎችን ለማፍራት የሚያስችልና የህብረተሰቡን አመለካከት ወደ እድገት አቅጣጫ የሚመራ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር በማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ዕድገቶችን የሚያፋጥን መሣሪያ ነው፡፡

ይህንን የትምህርት ሥራ ውጤታማ ለማድረግና የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሳለጥ በየጊዜው አሰራሮችን ለማሻሻልና ለማዘመን በየትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ መምህራን ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ሚና ከፍተኛ በመሆኑምመምህራን እና የትምህርት አመራሮች ሙያዊ ሥነምግባርን በመላበስ ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡በዚህ ረገድ አልፎ አልፎ በመምህራንና በትምርት ቤት አመራሮች የሚስተዋሉ የዲሲፕሊን ግድፈቶች ይታያሉ፡፡

ስለሆነምአሁን በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎችን በመፈተሽ ወቅቱንየዋጀ ወጥነት ያለው መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ ፲፮ አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሠ) እና አንቀፅ ፳፪ ሠስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

<u>፩ አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የመምህራንና የትምህርት አመራር ሙያዊ የስነ-ምግባር፤የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ ቁጥር 161/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**<u>፪ ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩ **"ከተማ"**፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪ **"አስተዳደር"**፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፫ **"ቢሮ"**፡-ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

፬ **"ትምህርት ቤት"**፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ፣አንደኛ ደረጃ፣መካከለኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

፭ **"የትምህርት አመራር"**፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር የሚገኙ የትምህርት ተቋማትን የሚመሩ ምክትል ርዕሳነ መምህራን፤ ርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች ናቸው፡፡

፮ **"መምህር"**፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተቀጥረውበማስተማር ስራ ላይ የሚገኙናቸው፤

፯ **"ሙያዊ ሥነ-ምግባር"**፡-ማለት በሙያዊ መቼት ውስጥ የግለሰቦችን ባህሪ እና የውሳኔ አሰጣጥን የሚመሩ የሞራል መርሆዎችን እና እሴቶችን፤ የሥነ ምግባር ደንቦችን ማክበር እና ከፍተኛ የአቋም ደረጃዎችን መጠበቅን ታማኝነት፣እና በሁሉም ሙያዊ ግንኙነቶች ውስጥ ፍትሃዊነት መሆን ነው፡፡

፰ **ሴኩላር**፡-ማለት ትምህርት ቤቶች ከሃይማኖታዊ እና ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ነጻ መሆን የሆነ ነው፡፡

፱ **ተገልጋይ**፡-በትምህርት ቤት አገልግሎት የሚፈልጉ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች፣ ማህበረሰቡ፣ ልዩ ልዩ ተቋማት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**፫ <u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፬ <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኙ ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ ፤መካከለኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን እና የትምህርት አመራሮች/ ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች/ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፭ <u>የመመሪያው ዓላማ</u>**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ፤መካከለኛ ደረጃ ፤ ሁለተኛ ደረጃ እና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን እና የትምህርት አመራሮች/ ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች/ ሙያዊ የስነ-ምግባር፤የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ ፡፡

# ክፍል ሁለት

# መምህራን እና የትምህርት አመራሮች መብት እና የሚከተልዋቸው ሙያዊ የሥነ-ምግባሮች

**፮ <u>የመምህራን መብት በሙያዊ ስነ-ምግባር</u>**

፩ መምህራን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ እና እውቀትን እና እውነትን ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመከተል መብት አላቸው።ይህ የኮርስ ቁሳቁሶችን የመምረጥ መብትን ያጠቃልላል ፣ሥርዓተ-ትምህርት ንድፍ,እና በቀልን ሳይፈሩ ምሁራዊ ምርምር እና ውይይት ያድርጉ።

፪ መምህራን በባልደረቦቻቸው ፍትሃዊ እና በአክብሮት የመስተናገድ መብት አላቸው። አስተዳዳሪዎች፣እና ተማሪዎችይህም ደህንነቱ የተጠበቀ እና ደጋፊ የስራ አካባቢ የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።

፫ ከአድልዎ እና ትንኮሳ ጥበቃየፕሮፌሽናል ራስን በራስ ማስተዳደር፡ መምህራን በማስተማር ዘዴያቸው ሙያዊ ዳኝነትን የመጠቀም መብት አላቸው።የግምገማ ልምዶችእና የክፍል አስተዳደርለተማሪዎቻቸው እና ለሙያዊ ኃላፊነታቸው የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን የመወሰን ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል።

፬ መምህራን በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ፍትሃዊ እና ገለልተኛ የፍትህ ሂደት የማግኘት መብት አላቸው።

፭ መምህራን የአካዳሚክ ታማኝነትን የመጠበቅ እና ከተማሪዎቻቸው እና የስራ ባልደረቦቻቸው ተመሳሳይ ነገር የመጠበቅ መብት አላቸው።

፮ የመደራጀት ነፃነት፤ መምህራን ወደ ሙያዊ ድርጅቶች የመቀላቀል፤ በጋራ ድርድር ውስጥ መሳተፍ ፣እና አጸፋውን ሳይፈሩ ለሙያቸው ጥብቅና የመቆም መብት አላቸው።

## ፯ ሙያዊ የስነ-ምግባር

ማንኛውም መምህርና የትምህርት ቤት አመራር ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሙያዊ የሥነ-ምግባር ተግባራትንመላበስይኖርባቸዋል፡፡

፩ የመንግስትን ፖሊሲ፣የትምህርት ፕሮግራሞችንና ዕቅዶችን በብቃት ይፈጽማሉ፡፡

፪ በሙያቸው ያምናሉ፤ሙያቸውን ያከብራሉ፤ይንከባከባሉ፡፡

፫ የኢትዮጰያና አለም አቀፍ ህጎች ፣ ደንቦች፣አዋጆችና መመሪያዎችን ያከብራሉ፡፡

፬ የተማሪዎችን አካዳሚክ ነጻነት(ማንኛውንምጥያቄ የመጠየቅ፣ማንኛውንም ሃሳብ የመግለጽና የማቅረብ) ይጠብቃሉ፡፡

፭ በሙያ ስነምግባራቸውና በብቁ ዜግነት ስብዕናቸው በአርአያነት ይቀርባሉ፡፡ በፀጉር አቆራረጣቸው ወይም በአሰራራቸው፣ በአለባበሳቸው እና በአነጋገራቸው በአጠቃላይ ሁለንተናዊ ስብዕናቸውበመልካም አርአያነት ይታያሉ፡፡

፮ ሲጋራ አያጨሱም፣ጫት አይቅሙም፣ አልኮሆል አይጠጡም፣ የተለያዩ ሱስ አምጪ እጾችን…ወዘተ አይጠቀሙም፡፡

፯ የፈተናን ሚስጥራዊነትን፣ አስተዳደርንና አሰራርንይጠብቃሉ፡፡

፰ ለተማሪዎቻቸው ተገቢውን ምክርና ክብር ይሰጣሉ፡፡

፱ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በተግባራዊ ጥናትና ምርምር ይፈታሉ፡፡

፲ ተማሪዎች ጤንነታቸውንና ደህንነታቸውን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

፲፩ ትምህርት ሴኩላር መሆኑን ተገንዝበው ተማሪዎችን ሲያስተምሩ ከስርዓተ ትምህርቱ ውጪ የግል አመለካከት/ሃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ/ ጉዳዮችን በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጭራሽ አያራምዱም፡፡

፲፪ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን መተላለፊያ መንገዳቸውን በመለየት እራሳቸውንና የትምህርት ማህበረሰቡን ይጠብቃሉ፡፡

፲፫ የአሰራር ህግና ደንብ በመከተል በተመደቡበት የስራ ቦታ ይሰራሉ፡፡

፲፬ አድመኝነትን ወይም አድማ ከሚመቱ ጋር አለመተባበር፡፡

፲፭ መደበኛ የሥራ ሰዓትን ሳይሸራርፉ በአግባቡ ሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

፲፮ የትምህርት ውስጣዊ  ብቃትን ለመጨመርበተነሳሽነት ይሰራሉ፡፡

፲፯ ጾታዊ ትንኮሳና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችበትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ እንዳይከሰቱ ይከላከላሉ፡፡

፲፰ ትምህርት የማህበረሰቡን ኑሮ ሊያሻሽል እንደሚችል በማመን ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን ትምህርት በየአካባቢያቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በተግባር እንዲፈቱበት ያደርጋሉ፡፡

፲፱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችልዩ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

፳ የተማሪዎችን ዝንባሌ እና ችሎታ፤የስነልቦናና የአካል እድገት ጠብቀው ትምህርቱን ይሰጣሉ፡፡

፳፩ በሰንደቅ ዓላማ ስነ-ሥርዓት ላይ ይገኛሉ ፣ ያስተባብራሉ፡፡

፳፪ በትምህርት ቤቱ እናበትምህርት ማህበረሰቡ መካከል የሚኖረው መልካም ግንኙነት ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

፳፫ የህጻናት መብት ድንጋጌዎችን ያከብራሉ፡፡

፳፬ ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ ይሰበስባሉ፣ ያደራጃሉ፤ይተነትናሉ፡፡ ተፈላጊውን መረጃ ይሰጣሉ፡፡

፳፭ የተማሪዎች የምገባ ሂደትን በቅርበት ይከታተላሉ፤ በምግብ ዝርዝሩ (ሜኑ) መሰረት እየተመገቡ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

፳፮ አዳዲስ አሰራሮችን ተቀብለው ይፈጽማሉ፡፡

፳፯ አዲስ ለሚመደቡ መምህራንና የትህርት ቤት አመራሮች ትውውቅ ያደርጋሉ፡፡ ልምድ ያካፍላሉ፡፡

፳፰ ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብታቸውን ያከብራሉ፡፡

፳፱ ለተማሪዎች ፣ ለሰራተኞችና ለተገልጋዮች ተገቢውን ክብር ይሰጣሉ፡፡

፴ ስራን ማዕከል ያደረገ ጤናማ ፣ግልጽነት ያለበት ግንኙነት ይፈጥራሉ፡፡

፴፩ በክበባት፣በዲፓርትመንት እና በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በመሳተፍና በማስተባበር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ ሌሎች የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

፴፪ በትምህርት ቤቱ ዙሪያ አዋኪ ጉዳዮች እንዳይኖሩ ያደርጋሉ፤ሲገኙም ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ችግሮቹን ይፈታሉ

# ክፍል ሦስት

## ዲሲፕሊን እርምጃዎች እና ውሳኔ አሰጣጥ

### ፰ <u>የዲሲፕሊን ቅጣት መሰረታዊ አላማ</u>

የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ የተቋሙን (የትምህርት ቤቱን) ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ሲሆን መምህርወይም የትምህርት አመራሩበፈጸመው ጥፋት ተጸጽቶ ወደፊት ብቁ እና ታማኝ ዜጋ ለመሆን እንዲችል ለመርዳት፣ ለማረምና ለማስተማር እንዲሁም የማይታረም በሚሆንበት ጊዜ ስራው እንዳይበደል ከስራ ለማሰናበት ነው፡፡

### ፱ <u>ስለ ዲሲፕሊን ቅጣት</u>

የዲሲፕሊን ጥፋት (ጉድለት) በፈጸመ ማንኛውም መምህር ወይም የትምህርት አመራር ላይ በአዋጅ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፰፱(፩) መሰረት እንደ ጥፋቱ ክብደት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፡፡

- ፩ የቃል ማስጠንቀቂያ፣
- ፪ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
- ፫ እስከ አስራ አምስት ቀን የሚደርስ የደመወዝ መቀጮ፣
- ፬ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የደመወዝ መቀጮ፣
- ፭ እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ከስራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣
- ፮ ከስራ ማሰናበት፣

### ፲ <u>የቅጣት አይነቶች አመዳደብ</u>

በዚህ መመሪያ በክፍል ሶስት በአንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፫ የተመለከቱት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ቅጣቶች ሲሆኑ ከንዑስ አንቀጽ ፬ እስከ ፮ የተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ቅጣቶች ተብለው የሚመደቡ ናቸው፡፡

### ፲፩ <u>ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

#### ፩ በመምህራን ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች

ሀ) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስራ መሳሪያዎችንና መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ አለመያዝ፡፡

ለ) ያለበቂ ምክንያት በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተው የስራ ሃላፊ ወይም አካል በወቅቱ አለማሳወቅ፡፡

ሐ) በቂ ባልሆነ ምክንያት የመማር ማስተማር የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች እና ውይይቶች ላይ አለመገኘት፣

መ) በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እና በክፍል ውስጥ ጋዋን አለመልበስና ባጅ አለማድረግ፣

ሠ) በመደበኛ የሥራ ሰዓት (፰ ሰዓት በቀን) ውስጥ ሌላ የግል ስራ መስራት ፤

ረ)በሰንደቅ ዓላማ ስነ-ሥርዓት ላይ አለመገኘት፣ አለማስተባበርና አለመዘመር፣

ሰ)በተለያዩ ምክንያቶች የባከኑ ክ/ጊዜዎችን እቅድ አውጥቶ ያለማካካስ ወይም እንዲካካሱ አለማድረግ፤

ሸ)በተጓዳኝ ክበባት ላይ በንቃት አለመሳተፍ

ቀ)የተማሪዎች የምገባ ሂደትን በሚወጣው መርሀ ግብር መሰረት በአግባቡ አለመከታተል

በ) ሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት አለማድረግ (የተመጠነ ማስታወሻ ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ወዘተ) አዘጋጅቶ አለማስተማር ፤

ተ) የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ አዲስ ጀማሪ መምህራን በአግባቡ አለመከታተል ፖርት ፎሊዮ አደራጅቶ አለመያዝ እና በተያዘለት ጊዜ አለማጠናቀቅ፤

ቸ) በተቀመጠው እቅድ መሰረት የእርስ በርስ  የክፍል ውስጥ ምልከታ አለማድረግ፤

ኀ) በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ተቋሙ ብልሹ አሰራር ወይም ድርጊት ሲፈጸም ተመልክቶ ያለማጋለጥ ፡፡

ነ) የወንድ መምህራን የፀጉር ርዝመት ከ፭(አምስት) ሴንቲ ሜትር ከበለጠ ፤

ኘ) የሴት መምህራን የፀጉር አሰራር ንጽህናውን ያልጠበቀና ለተማሪዎች መልካም አርዓያ ያልሆነ

አ) የወንድ መምህራን ሱሪ የተቀደደ ፣ የተተለተለ ፣ የቬል ስፋት ከ፮ (ስድስት) ሴንቲ ሜትር ያነሰ ከሆነ ፣ ነጠላ ጫማ ያደረገ

፪ **በርዕሳነ መምህራን ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች**

ሀ)ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ህጎች፣ ደንቦች ፤መመሪያዎች የስራ መሳሪያዎችንና መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ አለመያዝ፡፡

ለ)ለተገልጋይ የሚሰጠውን አገለግሎት በተቀመጠው ስታንዳርድ ጊዜ ፣ ጥራትና መጠን መሰረት አለመፈጸም፤

ሐ)ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ማለቃቸውን ወይም አለመሟላታቸውን እያወቀ ወይም በቸልተኝነት እንዲሟሉ አለማድረግ፡፡

መ)በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ተቋሙ ብልሹ አሰራር ወይም ድርጊት ሲፈጸም ተመልክቶ ያለማጋለጥ እና ያለማስቆም ፡፡

ሠ) የወንድ ፀጉር ርዝመት ከ፫ ሴ.ሜትር አስበልጦ ማሳደግ ፤

ረ) ንጽህናውን ያልጠበቀ የፀጉር አያያዝ

ሰ) ለወንድ ሱሪ የተቀደደ፣ የተተለተለ ፣የቤል ስፋት ከ06 ሴ.ሜትር ያነሰ መልበስ፣ ነጠላ ጫማ ማድረግ

ሸ) ለሴት ከጉልበት በላይ የሆነ ቀሚስ፣ እንብርት የሚያሳይ ቲ-ሸርት፣ የተተለተለ ሱሪ/ቀሚስ መልበስ ፣ የከንፈር ቀለም መቀባት፣

ቀ) ርዕሳነ መምህራን ከሆኑ ቦኃላ ማንኛውንም ዓይነት ንቅሳት (ታቱ) በሰውነት ላይ መነቀስ፣

በ) በዓመት ውስጥ የተቀመጠውን የትምህርት ክ/ጊዜ በአግበቡ ሥራ ላይ መዋሉን አለመከታተል

ተ) በመደበኛ የሥራ ሰዓት (ስምንት ሰዓት በቀን) ውስጥ ሌላ የግል ስራ መስራት፤መምህራኖች ሲሰሩ አለመከታተል

ቸ) በተለያዩ ምክንያቶች የባከኑ ክ/ጊዜዎችን እቅድ አውጥቶ እንዲካካሱ አለማድረግ፤

ኀ) መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ በቂ እገዛና ክትትል አለማድረግ፤

ነ) በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ጋዋን አለመልበስ፣

ኘ) በተቀመጠው እቅድ መሰረት የክፍል ውስጥ ምልከታ አለማድረግ፤

አ) የት/ቤቱን ዓመታዊ እቅድ በወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፉ ማቀድ ፤

ከ) ትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ተቋም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ የአሰራር ስርዓት፤ ቅድመ ሁኔታ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ለተገልጋዮች ግልጽ አለማድረግ፡፡

ኸ)በተቀመጠው እቅድ መሰረት ድጋፍና ክትትል አለማድረግ፤

ወ)በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት /መስተጋብር/ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን አለማድረግ ፤

ዐ) የመምህራንን ክፍተት እየለዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና አለመስጠት ወይም እንዲሰጥ አለማድረግ፤

ዘ) ከወላጅ ወይም ከማንኛውም ሌላ ተገልጋይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን በማጣራት አፋጣኝ እና አጥጋቢ ውሳኔ ወይም ምላሽ አለመስጠት፡፡

ዘ) የእቅድ አፈጻጸም ተግባራት ስራዎችን ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ አለመላክ

የ)በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ቀላል አስተዳደራዊ ጥፋቶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውን ሌሎች ጥፋቶች መፈጸም ናቸው፡፡

**፫ በሱፐርቫይዘር ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች**

ሀ)የመምህራንን ክፍተት እየለዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና አለመስጠት

ለ)ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ህጎች፣ ደንቦች ፤መመሪያዎች የስራ መሳሪያዎችንና መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ አለመያዝ፡፡

ሐ)የወንድ ፀጉር ርዝመት ከ፭ (አምስት) ሴ.ሜትር አስበልጦ ማሳደግ ፤

መ) ለሴት የፀጉር አሰራር ንጽህናውን ያልጠበቀና ለተማሪዎች መልካም አርዓያ ያልሆነ

ሠ) ለወንድ ሱሪ የተቀደደ፣ የተተለተለ፣ የቤል ስፋት ከ06 ሴ.ሜትር ያነሰ መልበስ፣ ነጠላ ጫማ ማድረግ ፣

ረ) ለሴት ከጉልበት በላይ የሆነ ቀሚስ፣ እንብርት የሚያሳይ ቲ-ሸርት የተተለተለ ሱሪ/ቀሚስ መልበስ ፣ የከንፈር ቀለም መቀባት፣

ሰ) ሱተርቫይዘር ከሆኑ ቦሃላ ማንኛውንም ዓይነት ንቅሳት (ታቱ) በሰውነት ላይ መነቀስ

ሸ) በዓመት ውስጥ የተቀመጠውን የትምህርት ክ/ጊዜ በአግበቡ ሥራ ላይ መዋሉን አለመከታተል

ቀ) መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ በቂ ክትትል አለማድረግ

በ) የት/ቤቱን ዓመታዊ እቅድ በወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፉ ማቀድ ፤

ተ) በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት /መስተጋብር/ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን አለማድረግ ፤

ቸ) የእቅድ አፈጻጸም ተግባራት ስራዎችን ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ አለመላክ ፤ወይም

ኀ) በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ቀላል አስተዳደራዊ ጥፋቶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውን ሌሎች ጥፋቶች መፈጸም ናቸው፡፡

**<u>፲፪ በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>**

፩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ ስነስርዓት በደንብ ቁጥር ፳፬ ሺ፪ሺ፪ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ በተገለጸው መሰረት የት/ቤቱ ወይም የተቋሙ ኃላፊ ወይንም የሚመለከተው የበላይ ኃላፊ አንድ መምህር

ወይም የትምህርት ቤት አመራር ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ እንደየጥፋቱ ክብደት የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠትና እስከ ፲፭ (አስራ አምስት ቀን) ደመወዝ የመቅጣት ስልጣንና ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

፪ በተወሰነው ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ያልተስማማ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ቅሬታውን ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ እና ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቅደም ተከተል ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፲፫ <u>የከባድ ዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

### ፩ በመምህራን ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች

ሀ)የበላይ ኃላፊ ትዕዛዝ ባለማክበር ፤ በቸልተኝነት ፣ በመለገም ፣ ወይም ሆነ ብሎ የአሰራር ሥነ- ስርኣት ወይም የመንግስትን ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል ማድረስ፤

ለ)ጉዳዮችን ሆነ ብሎ ማዘግየት ወይም ባለጉዳዮችን ማጉላላት ወይም ማመላለስ፤

ሐ)ተገልጋዩ ህብረተሰብ ወይም ባለጉዳዮችን በአግባቡ አለማስተናገድ ፣ ማመነጫጨቅ ፣ መሳደብ ወይም ተገቢውን አክብሮት አለመስጠት፤

መ)የተገልጋዩን ሰነድ ወይም ማህደር ሆነ ብሎ መደበቅ ወይም በቸልተኝነት እንዲጠፋ ማድረግ፤

ሠ) ለተገልጋዩ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ አድሎ መፈጸም፣

ረ)ስራ እንዳይሰራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

ሰ)ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ እንዳይፈጸሙ እንቅፋት መሆን፤

ሸ)አካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ ቅጣት በተማሪዎች ላይ ማድረስ፣

ቀ)በስራ ቦታ ጠብ መጫር መደባደብና አንባጓሮ መፍጠር፤

በ)በስካር ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ በስራ ቦታ ላይ መገኘት፤

ተ)ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ ወይም ለሌላ ሰው ጉቦን ማቀባበል ወይም መደለያ መቀበል ወይም መጠየቅ፤

ቸ)የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም፤

ኀ)በስራ ቦታ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

ነ)በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ተቋሙ ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፡፡

ኘ) አድመኝነት ወይም አድማ ከሚያደርጉ ጋር መተባበር፣

አ) በስልጣን አለአግባብ መጠቀም፤

ከ) በስራ ቦታ ላይ ጾታዊ ጥቃትና ትንኮሳ መፈጸም፡፡

ኸ) በህግ ወይም በአሰራር የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት መሸሽ ወይም አለመቀበል

ወ) የትምህርት ቤቱን ንብረት መሸሸግ፣መደበቅ ፣ማባከን፣ ያለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣ በጥንቃቄ ያለመያዝ ወይም በቸልተኝነት ለብልሽት እንዲደረጉ ማድረግ

ዐ) የትምህርት ቤቱን ወይም የትምህርት ተቋሙን ሃብትና ንብረት ለማይመለከተው አካል አሳልፎ መስጠት ፡፡

ዘ) የመማር ማስተማር ስራን የሚያደናቅፉ ተግባራትን መፈጸም፡፡

ዠ) ለዓመት የተሰጠውን ክፍለ ጊዜ በወቅቱ አለማጠናቀቅ

የ) የፈተናን ሚስጥራዊነትን አለመጠበቅ ፣

ደ) ትምህርት ሴኩላር መሆኑን በመገንዘብ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ወይም ሲደረግ በቸልተኝነት መመልከት

ጀ) ማንኛውንም የፖለቲካ አመለካከት በትምህር ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥም ሆነ በት/ቤት አካባቢ ማራመድ፣

ገ) የማንኛውም ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መገለጫ የሆኑትን ዓርማ ይዞ መገኘት፣አልባሳትን መልበስ፣ውይይት ቅስቀሳ የመሳሰሉትን ማካሄድ፣

ጠ) የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ ጽንፈኝነት አስተሳሰብን በሌላው ላይ በሃይል መጫን፣

ጨ) በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የግል የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት አቋም በመያዝ ግጭት ወይም ብጥብጥ እንዲነሳ ሙከራ ማድረግ ወይም መፈጸም፣

ጰ) ከህገ ወጥ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መረጃ መስጠት፣

ጸ) መንግስት በአሸባሪነት ከፈረጃቸው ህገ ወጥ ግለሰቦች ፣ቡድኖች እና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣

ፀ)ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን (ኤች አይቪ ኤድስ፣ ኮቪድ-ወዘተ) መተላለፊያ መንገዳቸውን እያወቀ በትምህርት ማህበረሰቡ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት እንዲደርስ ተባባሪ መሆን ፣

ፈ) በተደጋጋሚ በተሰጡ ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እርምጃዎች አለመታረም

ፐ) በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለውን ሌላ የዲሲፕሊን ጉድለት መፈጸም፣

## ፪ በርዕሳነ መምህራን ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች

ሀ)የበላይ ኃላፊ ትዕዛዝ ባለማክበር፤ በቸልተኝነት፣ በመለገም ፣ ወይም ሆን ብሎ የአሰራር ሥነ- ስርአት ወይም የመንግስትን ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል ማድረስ ሲደርስ መመልከት

ለ)የተገልጋዩን ሰነድ ወይም ማህደር ሆን ብሎ መደበቅ ወይም በቸልተኝነት እንዲጠፋ ማድረግ

ሐ)ተገልጋዩ ህብረተሰብ ወይም ባለጉዳዮችን በአግባቡ አለማስተናገድ ፣ ማመነጫጨቅ ፣ መሳደብ ወይም ተገቢውን አክብሮት አለመስጠት እና የተዘረዘሩት ሲፈጸሙ ማየት

መ)ስራ እንዳይሰራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

ሠ) ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ እንዳይፈጸሙ እንቅፋት መፍጠር ወይም ከመፈጸም መቆጠብ

ረ) አካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ ቅጣት በተማሪዎች ላይ ማድረስ ወይም ሲደርስ መመልከት፤ በስራ ቦታ ጠብ መጫር መደባደብና አንባጓሮ መፍጠር ወይም ሲፈጠር መፈትሄ አለመስጠት፤ተገልጋዩ መክፈል የማይገባውን የአገልግሎት ክፍያ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት እንዲከፍል ማድረግ፤

ሰ)በየደረጃው ካሉ አመራሮች ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ለሚሰጡ ህጋዊ ትዕዛዞች አፋጣኝ ምላሽ ያለመስጠትና ያለመፈጸም፡፡

ሸ)በስካር ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ በስራ ቦታ ላይ መገኘት ወይም በሚገኙት ላይ ክትትል እና እርምጃ አለመውሰድ፤

ቀ)ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ ወይም ለሌላ ሰው ጉቦን ማቀባበል ወይም መደለያ መቀበል ወይም መጠየቅ፡፤የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም ወይም ሲፈጸም ለህግ አለማቅረብ፤በስልጣን አለአግባብ መጠቀም፤

በ)በስራ ቦታ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም ሲፈጸም መመልከት፤

ተ)በመንግስት ስራ የተሳሳተ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በመስጠት በመንግስት ወይም በተገልጋዩ ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ማድረግ፤

ቸ)በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ተቋሙ ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ጉዳት በሚያደርሱት ላይ እርምጃ አለመውሰድ፡፡

ኀ)በስራ ቦታ ላይ ጾታዊ ጥቃትና ትንኮሳ መፈጸም ወይም ሲፈጸም ለህግ አካል አለማቅረብ፤

ነ)በተማሪዎች ምዝገባ ወቅት ከወላጆች ላይ የመመዝገቢያ ገንዘብ መሰብሰብ ፤በህግ ወይም በአሰራር የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት መሸሽ ወይም አለመቀበል፤

ኘ)በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የግል የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት አቋም በመያዝ ግጭት ወይም ብጥብጥ እንዲነሳ ሙከራ ማድረግ ወይም መፈጸም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምጃ አለመውሰድ

አ)ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን (ኤች አይቪ ኤድስ ፣ ኮቪድ… ወዘተ) መተላለፊያ መንገዳቸውን፤ እያወቀ በትምህርት ማህበረሰቡ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት እንዲደርስ ተባባሪ መሆን

ከ)ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ ለሚመለከተው አካል አለመስጠት ወይም በማይሰጡት ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ፤

ኸ)የትምህርት ቤቱን ክፍተት ለመሙላት ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ ከወላጆች፣መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ…ሀብትን አለማሰባሰብ

ወ)የመማር ማስተማር ስራን የሚያደናቅፉ ተግባራትን መፈጸም ወይም ሲፈጸም እርምጃ አለመውሰድ፤

ዐ)የማንኛውንም ፖለቲካ ፓርቲ መገለጫ የሆኑትን ዓርማ ይዞ መገኘት፤አልባሳትን መልበስ፤ውይይት ቅስቀሳ የመሳሰሉትን ማካሄድ ወይም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምጃ አለመውሰድ፤

ዘ)ትምህርት ሴኩላር መሆኑን በመገንዘብ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ እንቃስቃሴ ማድረግ ወይም ሲደረግ በቸልተኝነት መመልከት ፤የማንኛውም እምነት መገለጫ የሆኑትን ዓርማ ፤አልባሳት ወዘተ… የመሳሰሉትን ለብሶ ወይም ይዞ መገኘት ለብሰው ወይም ይዘው በተገኙት ላይ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፤

ዠ)በተደጋጋሚ በተሰጡ ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እርምጃዎች አለመታረም፤ለተገልጋዩ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ አድሎ መፈጸም፣

የ)ጉዳዮችን ሆነ ብሎ ማዘግየት ወይም ባለጉዳዮችን ማጉላላት ወይም ማመላለስ፤

ደ) የትምህርት ቤቱን ወይም የትምህርት ተቋሙን ሃብትና ንብረት ለማይመለከተው አካል አሳልፎ መስጠት፤የት/ቤቱን ወይም የትምህርት ተቋሙን ህጋዊ ሰነዶችና መረጃዎችን ማጥፋት፤ ማበላሸት ወይም መሰወር፤

ጀ)የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ ጽንፈኝነት አስተሳሰብን በሌላወ ላይ በሃይል ተጽእኖ መፍጠር ወይም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምት አለመውሰድ፤ከጽንፈኛ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መረጃ መስጠት፤መንግስት በአሸባሪነት ከፈረጃቸው ግለሰቦች ፤ቡድኖች እና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፤

ገ)ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሆነ ሪፖርት አለማቅረብ፡፡

ጠ) በመደበኛ የሥራ ሰዓት (ስምንት ሰዓት በቀን) ውስጥ ሌላ የግል ስራ መስራት እና መምህራን ሲሰሩ አለመከታተል፤ ያሉትን መምራን መሰረት ያደረገ የክፍለ ጊዜ ድልድል በወቅቱ አለመስራት ፤

ጰ) ፈተና በሚፈትኑበት ወቅት ተማሪዎችን ከመከታተል ውጭ ፈተናን ሊያውክ የሚችል ማንኛውንም ተግባር እንዳይፈጸም አለመከታተል፤የፈተናን ሚስጥራዊነትን አለመጠበቅ ፤

ጸ)በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለውን ሌላ የዲሲፕሊን ጉድለት መፈጸም

ፀ)ዓመታዊና እለታዊ የትምህርት እቅድ በወቅቱ እንዲዘጋጅ ክትትል አለማድረግ ፤በዓመት ውስጥ የተቀመጠውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአግበቡ ሥራ ላይ መዋሉን አለመከታተል፤

ፈ)የትምህርት ቤቱን ንብረት መሸሸግ፤መደበቅ ፤ማባከን፤ ያለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፤ በጥንቃቄ ያለመያዝ ወይም በቸልተኝነት ለብልሽት እንዲደረጉ ማድረግ ይህንን በሚፈጽሙት ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ አለመውሰድ፤

ፐ)የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ አለመከታተልና ፖርት ፎሊዮ በአግባቡ አደራጅቶ አለመያዝ ፤መምህራንም የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እና አዲስ ጀማሪ መምህራን በአግባቡ እንዲከታተሉ ፤ፖርት ፎሊዮ አደራጅተው እንዲይዙ እና በተያዘለት ጊዜ እንዲያጠናቅቁ ድጋፍና ክትትል አለማድረግ

## ፫ በሱፐርቫይዘሮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች

ሀ) ትዕዛዝ ባለማክበር፤ በቸልተኝነት፣ በመለገም፣ ወይም ሆነ ብሎ የአሰራር ሥነ- ስርአት ወይም የመንግስትን ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል ማድረስ ሲደርስ መመልከት

ለ) ተገልጋዩ ህብረተሰብ ወይም ባለጉዳዮችን በአግባቡ አለማስተናገድ፣ ማመነጫጨቅ፣ መሳደብ ወይም ተገቢውን አክብሮት አለመስጠት፤

ሐ) የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ ጽንፈኝነት አስተሳሰብን በሌላው ላይ መጫን ውይም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምት አለመውሰድ

መ) በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የግል የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት አቋም በመያዝ ግጭት ወይም ብጥብጥ እንዲነሳ ሙከራ ማድረግ ወይም መፈጸም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምጃ አለመውሰድ

ሠ) ከጽንፈኛ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መረጃ መስጠት፤መንግስት በአሸባሪነት ከፈረጃቸው ግለሰቦች ፤ቡድኖች እና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፤

ረ) ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን (ኤች አይቪ ኤድስ፣ ኮቪድ-... ወዘተ) መተላለፊያ መንገዳቸውን እያወቀ በትምህርት ማህበረሰቡ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት እንዲደርስ ተባባሪ መሆን

ሰ) ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ ለሚመለከተው አካል አለመስጠት ወይም በመይሰጡት ላይ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ

ሸ) በተማሪዎች ምዝገባ ወቅት ከወላጆች ላይ የመመዝገቢያ ገንዘብ መሰብሰብ ፤ በተደጋጋሚ በተሰጡ ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እርምጃዎች አለመታረም

ቀ) የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም ወይም ሲፈጸም ለህግ አለማቅረብ፤ በስራ ቦታ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም ወይም ሲፈጸም መመልከት

በ) በስራ ቦታ ጠብ መጫር መደባደብና አንባጓሮ መፍጠር ወይም ሲፈጠር መፍትሄ አለመስጠት፤ስካር ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ በስራ ቦታ ላይ መገኘት ወይም በሚገኙት ላይ ክትትል አለማድረግ፤

ተ)አካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ ቅጣት በተማሪዎች ላይ ማድረስ ወይም ሲደርስ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረግ፤

ቸ)ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ ወይም ለሌላ ሰው ጉቦን ማቀባበል ወይም መደለያ መቀበል ወይም መጠየቅ፡፡

ኀ)በስልጣን አለአግባብ መጠቀም፤ በስራ ቦታ ላይ ጾታዊ ጥቃትና ትንኮሳ መፈጸም ወይም ሲፈጸም ለህግ አካል አለማቅረብ

ነ)የፈተናን ሚስጥራዊነትን አለመጠበቅ ፤በሚያስተባብሩበት ትምህርት ቤት ወይም ክላስተር ማእከል ብልሹ አሰራር ወይም ድርጊት ሲፈጸም ተመልክቶ ያለማጋለጥ

ኘ)በህግ ወይም በአሰራር የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት መሸሽ ወይም አለመቀበል፤የትምህርት ቤቱን ወይም የትምህርት ተቋሙን ሃብትና ንብረት ለማይመለከተው አካል አሳልፎ መስጠት፡፡

አ)ተገልጋዩ መክፈል የማይገባውን የአገልግሎት ክፍያ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት እንዲከፍል ሲደረግ እርምት አለመውሰድ

ከ)የመማር ማስተማር ስራን የሚያደናቅፉ ተግባራትን መፈጸም ወይም ሲፈጸም ማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ

ኸ)በየደረጃው ካሉ አመራሮች ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ለሚሰጡ ህጋዊ ትዕዛዞች አፋጣኝ ምላሽ ያለመስጠትና ያለመፈጸም፡፡

ወ)መምህራን የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እና አዲስ ጀማሪ መምህራን በአግባቡ እንዲከታሉ ፖርት ፎሊዮ አደራጅተው እንዲይዙ እና በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ክትትል አለማድረግ

ዐ)በተቀመጠው እቅድ መሰረት ድጋፍና ክትትል አለማድረግ፤ ትምህርት ሴኩላር መሆኑን በመገንዘብ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሃይማኖታዊም ሆነ ፖለቲካዊ እንቃስቃሴ ማድረግ ወይም ሲደረግ በቸልተኝነት መመልከት

ዘ) በትምህርት ቤት ውስጥ የተከለከሉ እምነት መገለጫ የሆኑትን ዓርማ ፤አልባሳት የመሳሰሉትን ለብሶ ወይም ይዞ መገኘት፤ ለብሰው ወይም ይዘው በተገኙት ላይ የእርምት ርምጃ አለመውሰድ

ዠ)የአንድን ፖለቲካ አመለካከት በትምህር ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ማራመድ በሚያራምዱት ላይ እርምጃ አለመውሰድ

የ)የአንድን ፖለቲካ ፓርቲ መገለጫ የሆኑትን ዓርማ ይዞ መገኘት፤አልባሳትን መልበስ፤ውይይት ቅስቀሳ የመሳሰሉትን ማካሄድ ወይም ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ እርምጃ አለመውሰድ

ደ)በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለውን ሌላ የዲሲፕሊን ጉድለት መፈጸም

ጀ)ለተገልጋዩ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ አድሎ መፈጸም፣ስራ እንዳይሰራ ሆነ ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፡፡

## ፲፬ <u>ከደረጃና ከደመወዝ ዝቅ በማድረግ የሚሰጥ የቅጣት አወሳሰን</u>

ማንኛውም መምህር፤ ሱፐርቫይዘር እና የት/ቤት አመራርበመንግስት ሰራተኞች አዋጅ፻፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፷፱ ንዑስ አንቀጽ፩(ሠ)መሰረት ከስራ፣ ደረጃና ከደመወዝ ዝቅ በማድረግ የትምህርት ተቋሙ ቅጣት ወስኖበት የቅጣቱ ጊዜ ገደብ እንዳለቀ፤

፩ የቅጣት ቆይታ ጊዜው ጨርሶ ሲመለስ ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የስራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ ክፍት የስራ ደረጃ ካለ ካለምንም ተጨማሪ ስነ-ስርዓት ወደ ስራ ደረጃው እንዲመለስ ይደረጋል፤

፪ ከመቀጣቱ በፊት ይዞት የነበረው የስራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የስራ ደረጃ ካልተገኘ ደሞዙ እየተከፈለው ክፍት የስራ ደረጃ በተገኘ ጊዜ ያለ ምንም ተጨማሪ ስነ-ስርዓት በስራ ደረጃው ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

## ፲፭ መምህር ወይም የትምህርት አመራርን ከስራና ከደሞዝ አግዶ ስለማቆየት

፩ አንድ መምህር ወይም የትምህርት አመራር ከስራ ሲታገድ የሚታገደው በአዋጅ ቁጥር አዋጅ፺፮/፪ሺ፲ መሰረት ይሆናል፡፡

፪ መምህሩ ወይም የትምህርት ቤት አመራሩን ከስራ አግዶ ማቆት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እግዱ የሚፈጸመው በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ይሆናል፣መምህሩ ወይም ምክትል ርእሰ መምህሩ የሚታገደው በትምህርት ቤቱ ዋና ር/መምህር ሲሆን ዋና ርዕሰ መምህርና ሱፐርቫይዘር የሚታገዱት በየደረጃው ባሉት በክ/ከተማ እና የወረዳ የትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊዎች ወይም ቤት ደረጃ ባሉ ሃላፊዎች ይሆናል፡፡

፫ ውሳኔ ሳያገኝ ከስድስት ወራት በላይ የቆየ መምህር ወይም የትምህርት አመራር ያለተጨማሪ ስነ ስርዓት በእግድ ወቅት ያልተከፈለውን ሙሉ ደሞዝ ያለወለድ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተገለጸው መሰረት የት/ቤቱን ወይም የትምህርት ተቋሙን መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ወደ ስራው ካልመለሰው በመምህሩ ወይም በትምህርት አመራሩ ላይ ለደረሰው መጉላላትና በደል ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

## ፲፮ መምህሩን ወይም የትምህርት አመራርን ከስራ ሲታገድ የሚኖረው አፈጻጸም

፩ በአዋጅ ቁጥር ፺፮/፪ሺ፲ በአንቀጽ ፸፪ ንዑስ ቁጥር ፫ መሰረት ከሥራና ደመወዝ የታገደ መምህር፣ ም/ርዕሰ መምህር፣ ር/መምህር፣ ሱፐርቫይዘር ከመደበኛ ሥራው ታግዶ የሚቆይበት ጊዜና ከሥራው የታገደበት ምክንያት እግዱን በሰጠው ስልጣን ባለው ሀላፊ ወይም የበላይ ሀላፊ በጽሁፍ ይገለጽለታል፡፡

፪ ዕግድ የተደረገበት መምህር፣ ም/ርዕሰ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር አድራሻው ያልታወቀ እንደሆነ ትዕዛዙ በሚሰራበት ትምህርት ቤት ወይም የትምህረት ተቋም የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለአስር ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

፫ ከስራ መታገዱ የሚጸናው የማገጃ ትዕዛዝ በጽሁፍ ከተሰጠው ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

፬ መምህሩ ወይም የትምህርት አመራሩ በተከሰሰበት ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግዱ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደሞዙ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

፭ የዲሲፕሊን ቅጣቱ ውሳኔ የገንዘብ ቅጣት ከሆነ ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ (1/3) ሳይበልጥ የሚቆረጥ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነውም መምህሩ ወይም የትምህርት አመራሩ ወደ ስራ ከተመለሰበት ቀጣዩ ወር ጀምሮ ይሆናል፡፡

፮ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ከሥራ በመታገድ ምክንያት ከዕግዱ ጋር ያልተያያዙ ሌሎች መብቶቹንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

**፲፮ የቅጣት ቅደም ተከተሉን ባለመጠበቅ ስለሚሰጥ ውሳኔ**

በዚህ መመሪያ የተፈጸመው የዲሲፕሊን ጥፋት ክብደት ተመዝኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9ስር ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች መካከል ቅደም ተከተሉ ሳይጠበቅ አንዱን ለመወሰን ይቻላል፡

# ክፍል አራት

## ስለ ዲሲፕሊን ኮሚቴ መቋቋም፤ አባለት፤ የአባላት መመዘኛ እና አገልገሎት ጊዜ

**፲፯ ስለ መቋቋምና አባላት**

**፩ ስለ መቋቋም**

በደንብ ቁጥር ፸፮/፲፬ መሰረት በየትምህርት ቤቱ ወይም በየትምህርት ተቋሙ የዲሲፒሊን ጉዳዮችን እየመረመረ የውሳኔ ሃሳብ እንደየትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ተቋሙ ተጠሪነት ለትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር ወይም ምክትል ርዕስ መምህር ወይም ለተቋሙ ሃላፊ ወይም ለሚወክለው ወይም ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ወይም ለክፍለ ከተማው ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ለሚወክለው የሚያቀርብ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

**፪ አባላት**

የኮሚቴው አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. በርዕሰ መምህር ወይም በተቋሙ ኃላፊ የሚሰየም አንድ ሰው---------------------------- ሰብሳቢ

ለ. በርዕሰ መምህር ወይም በተቋሙ ኃላፊ የሚሰየም አንድሰው ------------------------------ አባል

ሐ. ከትምህርት ተቋሙ መሰረታዊ የመምህራን ማህበር የሚወከል አንድ ተወካይ ----------አባል

መ. ከትምህረት ተቋሙ መሰረታዊ የመምህራን ማህበር የሥርዓተ ጾታ ዘርፍ ተጠሪ አንድ ሴት መምህርት ------------አባል

ሠ. የወላጅ፣የተማሪ፣መምህር ህብረት/ወላጅ፤ተማሪ፤መመህር ህበረት ተወካይመካከል አንድ ተወካይ-----አባል

ረ. የትምህረት ተቋሙ የሰው ኃይል አስተዳደር ተወካይ ---------------------------አባልና ጸሀፊ

፲፱ **አባልነት መመዘኛና አገልገሎት ዘመን**

**፩ አባልነት መመዘኛ**

ማናቸውም የኮሚቴ አባል፡-

ሀ) በጠባዩና በስራ አፈጻጸሙ የተመሰገነ፣

ለ) ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ያልተቀጣ፣

ሐ) ቋሚ መምህርየሆነና በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ተቋሙ ግቢ ውስጥ ቢቻል ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

**፪ የአገልግሎት ዘመን**

ሀ) የተመረጡት የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

ለ) የዚህ አንቀጽ ፪(ሀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአንድ ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሁሉም ወይም በከፊል ሊመረጡ ይችላሉ

፳ **ከአባልነት ስለመሰረዝ እና ከስብሰባ ስለመነሳት**

ሀ) የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም አባል ክስ ከቀረበበት መምህር ጋር ፀብ ያለው ወይም በስጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ ወይም ከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ለዚያ ጉዳይ ብቻ ከኮሚቴው አባልነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተገለፀው መሰረት የኮሚቴ ሰብሳቢው ከሰብሳቢነት የሚነሳ ከሆነ የቀሩት የኮሚቴ አባላት ከመሃከላቸው ለዚህ ብቻ ሌላ ሰብሳቢ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡

ሐ) ማንኛውም የኮሚቴ አባል በግል ችግር ምክንያት በኮሚቴው ያለውን ተሳትፎ መቀጠል ሳይችል ሲቀር፣ከመስሪያቤት ሲለቅ፤በተለያየ ምክንያት ስራውን በአግባቡ ማከናወን አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤ራሱን ከጉዳዩ በማግለልና ሌላውን አባል ለማስጠላት የሞከረ ወይም ሚስጥር ያወጣ ወይም ቃለጉ ባኤዎችን መረጃዎችንና ጽሁፎችን ለተከሳሹ ያሳየ ወይም ያጋለጠ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤በዚህ መመሪያ ከባድ ጥፋት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን እንደፈጸመ ተቆጥሮ የሚወሰደው የዲሲፕሊን የቅጣት አፈጻጸም እንደተጠበቀ ሆኖ ከኮሚቴው አባልነት ይሰረዛል፡፡ በምትኩም ስልጣን ባለው ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊ እንዲሰየም ይደረጋል፡፡

መ) ከኮሚቴ አባልነት በተሰረዘ አባል ምትክ የተሰረዘው የኮሚቴ አባል በተመረጠበት ወይም በተመደበበት መንገድ አዲስ ሌላ አባል ይተካል፡፡

**፳፩ <u>የኮሚቴው ምልአተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ</u>**

ሀ) በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከግማሽ አባላት በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤ ከተገኙ አባላት ቢያንስ አንዱ የመምህራን ተወካይ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ) የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢቀር የቀሩት አባላት ከመካከላቸው ለጊዜው ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡

ሐ) ማንኛውም የኮሚቴው ውሳኔ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡እኩል ድምጽ ሲሆን ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፤የልዩነት ሀሳብ በቃለ ጉባኤ ይሰፍራል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ዲሲፕሊን ክስ፤ምርመራ እና አሰራር

**፳፪ <u>ስለ ዲሲፕሊን ክስ አመሰራረት</u>**

፩ የዲሲፕሊን ክስ የሚመሰረተው በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህርወይም ምክትል ርዕሰ መምህር በኩል የሰው ኃይል አስተዳደር አማካይነት የዲሲፕሊን ክሱን ይመሰረታል፤

፪ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ሰብሳቢ በሰው ሃብት አስተዳደር በኩል የዲሲፕሊን ክስ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ለተከሳሽ መጥሪያ ይልካል፡፡

፫ የሚላከው መጥሪያ ተከሳሹ ለተጠረጠረበት ዝርዝር ጥፋት በዲሲፕሊን ኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚያቀርብበትን ቀን፣ ሰአትና ቦታ በመግለጽ ክሱን በጽሁፍ ማስረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

፬ ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስና የመከላከያ ማስረጃ የሚያቀርብበት ጊዜ የክሱ ጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ከሶስት ቀን ማነስ የለበትም፡፡

፭ የተከሳሹ አድራሻ ያልታወቀ እንደሆነ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚገኝበት ቀን ሰአትና ቦታ ተገልጾ የጥሪ ማስታወቂያ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ተከሳሹ በተወሰነው ጊዜ ካልቀረበ በሌለበት ክሱ ተሰምቶና ተመርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለትምህርት ቤቱ ር/መምህር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፯ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በከሳሽም ሆነ በተከሳሽ በኩል ጉዳዩ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ማሰባሰብን የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የውሳኔ ሃሳቡን ለር/መምህሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ፳፫ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አሰራር

፩ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ የሚያስፈልጉትን ማህደሮች፣ መረጃዎችና ሰነዶች አስቀርቦ ማየት እንዲሁም አግባብነት ያለውን የሰው ምስክር መጥራትና መስማት ይቻላል፡፡

፪ ኮሚቴው በመምህራንን ወይም በት/ቤት አመራርላይ የቀረበውን ክስ በሚያጣራበት ጊዜ

ሀ) የተከሳሹ ሙሉ ስም ከነ አያት

ለ) ተከሳሹ የተከሰሰበትን ጭብጥ

ሐ) ክሱን ያረጋግጣሉ ተብለው የቀረቡትን የጽሁፍም ሆነ የሰው ምስክርነት ማስረጃዎች፣

መ) በትምህርት ተቋሙ ውስጥ የሚገኘውን የተከሳሹን የግል ማህደር እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተከሳሹ በሌላ ቦታ ተቀጥሮ ያገለገለ ከሆነ ቀደሞ ይሰራበት ከነበረው የትምህርት ተቋም የሚገኘውን የግል ማህደር፣

ሠ) ለቀረበው ክስ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦችና፣ መመሪያዎች

ረ) ሰራተኛው ማስረጃዎች ናቸው ብሎ የሚያቀርባቸውን የጽሁፍና የሰው ማስረጃዎች፤

ሸ) ከላይ ከተመለከቱት ውጭ ሌሎች አግባብነት አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን ማስረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ በማስቀረብ መመርመር ይቻላል፡፡

## ፳፬ ኮሚቴው የቀረበውን ክስ በማስረጃ በሚያጣራበት ጊዜ

፩ ለተከሳሹ ክሱና ማስረጃው በጽሁፍ እንዲደርሰውና የመከላከያ መልሶችን በጽሁፍ የማቅረብ መብት እንዲጠበቅለት

፪ የከሳሹ ምስክሮች ሲቀርቡ ተከሳሹ በተገኘበት ቃላቸውን እንዲሰጡና ተከሳሹም የሚፈልገውን የመስቀለኛ ጥያቄ እንዲያቀርብ እንዲሁም የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ ከሳሽ ተገኝቶ የመስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅለት፣

፫ ተከሳሹ የመደመጥ፣ የመከራከርና በበኩሉ የመከላከያ ማስረጃዎችና ክርክሮቹንም የማቅረብ መብቱ ተጠብቆ ክሱ በማስረጃ እንዲጣራ የማድረግ፣

፬ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ከደረሰው የዲሲፕሊን ጉደለት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆንና ለተመሳሳይ ጥፋትም ተመሳሳይ ቅጣት እንዲሰጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ፳፭ ለዲሲፕሊን ኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ በቃለ ጉባኤ ፀሐፊ በኩል የሚከናወን ተግባራት፡፡

፩ የዕለታዊ አጀንዳ ቅደም ተከተል በዕለቱ ለይቶ የመያዝ

፪ የስብሰባው ቃለ ጉባኤ በትክክል እየተጻፈና እየተዘጋጀ አባላቱም እንዲፈርሙበት ሆኖ በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፤

፫ ከሳሽና ተከሳሽ እንዲሁም ምስክሮች የሚሰጡትን ቃል በትክክልና በጥንቃቄ መመዝገብና ቃል ሰጭዎች በስብሰባው መጨረሻ ላይ እንዲፈርሙበት መደረግ አለበት፡፡

፬ በሁለቱም ወገን የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተመዝግበውና ለኮሚቴው ቀርበው ከታዩ በኋላ ፋይሉን አደራጅቶ በጥንቃቄ ማስቀመጥ አለበት፤

፭ ለተከራካሪ ወገኖች፣ለምስክሮችና ለሌሎች አስረጂዎች የሚሰጡ መጥሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ደብዳቤዎች የተዘጋጁና ሰብሳቢው እየፈረመባቸው ለሚመለከተው ሰው ወይም መስሪያ ቤት መላካቸውን ወይም መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣

፮ በማስታወቂያ በሚወጡ ጽሁፎች በተገቢው ቦታ መለጠፋቸውን ወይም ለሚመለከተው ሰው ወይም ክፍል መድረሳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፳፮ ለዲሲፕሊን ኮሚቴው ስለሚቀርቡ የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች

፩ ተከሳሹ ተነገረበት ለጥፋት ማፍረሻ ወይም መከላከያ የሚሆነውን ተፈቅዶ በስራ ላይ የነበረ ወይም ያለ አሰራር ደንብ ወይም ሌላ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ምስክሮች ማቅረብ ይችላል፡፡

፪ ተከሳሹ እንዲቀርብለት ወይም ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቃቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች፣ደንቦች በትምህርት ተቋሙ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ከጭብጡ ጋር አግባብነት ያላቸው መሆኑን ሲያምንበት እንዲቀርብ የሚመለከተውን ክፍል ወይም ተቋም ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፫ ማንኛውም፣ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ተቋም በኮሚቴው ሲጠየቅ ተፈላጊዎቹን ህጎች፣ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሌሎች የጽሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማሳየት ወይም ትክክል ግልባጩን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፬ ተከሳሹ ጭብጡን የሚያስረዱለት ምስክሮች እንዲጠሩለት ስማቸውንና አድራሻቸውን ዘርዝሮ ጥያቄውን ካቀረበ ኮሚቴው እንዲጠሩና ቀርበው እንዲመሰክሩ ለማድረግ ይቻላል፡፡

## ፳፯ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ

፩ ኮሚቴው የቀረበለትን የከባድ የዲሲፕሊን ክስ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ አቅርቦ በኃላፊው እንዲወሰን ያደርጋል ፤ የዲሲፕሊን ክስ ለኮሚቴው ሲቀርብ ኮሚቴው ጉዳዩ በደንብ ቁጥር ፴፯ መሰረት ክሱ አዋጅ፶፮/፪ሺ፲ አንቀፅ ፴፫ መሰረት በይርጋ የታገዱ ከሆኑ ወይም ተፈጸመ የተባለው ድርጊት በዲሲፕሊን ሊያስከስስ የማይችል ከሆነ ወይም በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ተከሳሹ በነዚህ ጉዳዮች

ላይ ተከሳሹ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ካነሳና ከተከራከረ ክሱን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

፪ በምርመራው ውጤት ላይ ተመስርቶ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የቀረበለት የዲሲፕሊን ጉዳይ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ውድቅ መሆኑን ከነምክንያቱ በመዘርዘር የውሳኔ ሃሳብ ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

፫ የቀረበው ክስ በሙሉ ወይም በከፊል በማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ እንደ ነገሩ ክብደት ለተፈጸመው ጥፋት ተመጣጣኝ የሆነ የዲሲፕን ቅጣት በዚሁ መመሪያ አንቀፅ ፱ (፬) እስከ ፱(፮) ከተዘረዘሩት የዲሲፕሊን ቅጣቶች ውስጥ አንዱን ቅጣት የውሳኔ ሀሳብ ለሚመለከተው የበላይ ሃላፊ ያቀርባል፡፡

፬ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ በሚመለከተው ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተሰጥቶበት በጽሁፍ ለተከሳሽ እስኪሰጥ ድረስ በሚስጢር መጠበቅ አለበት፡፡

፭ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከሳሹ በጽሁፍ እንዲሰጠው መደረግ አለበት፡፡

፮ በአዋጅ፶፮/፪ሺ፲ መሰረት በትውስት የተዛወረ መምህር ወይም የት/ቤት አመራር የዲሲፕሊን ጉዳይ በቀጣሪው ትምህርት ቤት ወይም ተቋም የሚታይና የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፳፭ ውሳኔ አሰጣጥ

በመምህራን ወይም የት/ቤት አመራር ላይ የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ በዚህ መመሪያ ስልጣን የተሰጠው የሚመለከተው ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊ በዲሲፕሊን ኮሚቴው ተጣርቶ የሚቀርብለትን የዲሲፕሊን ቅጣት የውሳኔ ሃሳብ በማጽደቅ ወይም በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ፳፱ የዲሲፕሊን ቅጣት አወሳሰን

፩ በዚህ የዲሲፕሊን ኮሚቴ መመሪያ ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ ፲፭/፪ በተቋቋመው ኮሚቴ ታይቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብ ሲሆን በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ውሳኔ መስጠት የሚችለው በትምህርት ቤቱ አመራር (ርዕሰ መምህር፣ ም/ርዕሰ መምህር ወይም በሚወከለው ኃላፊ) ይሆናል፡፡

ሀ/ ለወረዳ ተጠሪ የሆነ ትምህርት ቤትአመራር በወረዳው ት/ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም በሚወከለው ኃላፊ ይሆናል፡፡

ለ/ ለክፍለ ከተማው ተጠሪ የሆነ ትምህርት ቤትአመራር ለክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት ሃላፊ ወይም በሚወክለው ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪ በዲሲፕሊን የሚወሰን ቅጣት የማናቸውንም ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔ አለመጠበቁ በዲሲፕሊን የሚወሰነው ቅጣት የማናቸውም ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔ ስለማይከተል ስለዲሲፕሊን ጉድለት አፈጻጸም በዚህ መመሪያ የተገለጸውን በመከተል የፍ/ቤት ወይም የሌላ መስሪያ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ራሱን በቻለ ተለይቶና ተጣርቶ መወሰን አለበት ፡፡

፫ የዲሲፕሊን ቅጣት በሪከርድነት ስለሚቀይበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፲ አንቀጽ ፷፱ንዑስ አንቀጽ (፰) መሰረትይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

# የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት

**፴ ዓላማ**

የቅሬታዎች የማስተናገጃ ስነ-ስርዓት ዓላማ፡-

፩ ለቅሬታዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣

፪ ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን በማረም እና

፫ ሁሉንም በኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችልና ፍትሀዊ የሆነ አሰራር በማስፈን የሰመረ የሰራተኛ ግንኙነት እንዲዳብር ማድረግ ነው ፡፡

**፴፩ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

፩ በማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ተቋም መምህርን፤የት/ቤት አመራርን እና የትምህርት ተቋም ሃላፊ የሚያቀርበውን የቅሬታ አቤቱታ ተቀብሎ በመመርመር ስልጣን ላለው ኃላፊ ወይም የበላይ ሀላፊ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

፪ ሆኖም የዲሲፒሊን ኮሚቴ አባል የሆነ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሊሰየም /ሊወከል/ አይችልም፡፡

**፴፪ አባላት**

፩ የመምህራን ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አወቃቀር

ሀ. በርዕሰ መምህር ወይም የተቋም ኃላፊ የሚሰየም …………… ሰብሳቢ

ለ. በርዕሰ መምህር ወይም የተቋም ኃላፊ የሚሰየም …………. አንድ አባል

ሐ. ከት/ቤቱመሰረታዊ መምህራን የሚመረጡ ሁለት ተወካዮች፡-(አንድ የመ/ራን ማህበር ተወካይና አንድ ከመሰረታዊ መ/ማ/የሥ/ጾታ ተጠሪ ሴት መ/ት) --------አባል

መ. ከወላጅ ፣ የተማሪ ፣ መምህር ህብረት (ወተመህ ምክር ቤት) አንድ የወላጅና አንድ የተማሪ ተወካይ ሁለት ……አባል

ሠ. የት/ቤቱ የሰው ሃይል አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት መሪ …አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

፪ የትምህርት ቤትአመራር የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አወቃቀር

ሀ. በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ወይም በክፍለ ከተማት/ጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰየም----ሰብሳቢ

ለ. በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ወይም በክፍለከተማት/ጽ/ቤት የሚሰየም -------አባል

ሐ. ከት/ተቋሙ መሰረታዊ መ/መምህራን ተወካይና የሥርአተ ጾታ ተጠሪ ሁለት ተወካዮች፡----አባል

መ. ከወላጅ ፣ የተማሪ ፣ መምህር ህብረት (ወተመህ) ተወመ ምክር ቤት አንድ የተማሪ አንድ የወላጅና ተወካይ ሁለት ………አባል

ሠ. የት/ተቋሙ የሰው ሃይል አስተዳደር ደጋ የስራ ሂደት መሪ …….አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

፫ በበላይ ሃላፊው ስለሚሰየሙ አባላት አሰያየም

በዚህ አንቀጽ ፴፪(፪ (ሀ እና ለ) የተመለከቱት የኮሚቴው አባላት የሚሰየሙት ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ተቋሙ ይሆናል፡፡ሆኖም ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ተቋሙ የሚወክል በሚታጣበት ጊዜ ከሚመለከተው ኃላፊው ጽ/ቤት ሰራተኞች መካከል ሊሰየም ይችላል፡፡

## ፴፫ <u>አባልነት መመዘኛ</u>

ማናቸውም የኮሚቴ አባል፡-

፩ በመልካም ስነ ምግባሩና በስራ አፈጻጸሙ የተመሰገነ፣

፪ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ በዲሲፕሊን ጉድለት ያልተቀጣ፣

፫ ቋሚ የመንግስት ሰራተኞች የሆነና በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ከሁለት አመት በላይ አገልግሎት ያለው መሆን ይገባል፡፡

## ፴፬ <u>የአገልግሎት ዘመን</u>

፩ በሰራተኛ የተመረጡ የኮሚቴ አባለት የአገልግሎት ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፡፡ሆኖም የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ የመምህራን ተወካዮች እንደገና ለአንድ የአገልግሎት ዘመን ሊመደብ ወይም ሊመረጥ ይችላል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም የትምህርት ተቋሙ ሃላፊ ወይም በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ የሚመደቡ የኮሚቴ አባላት እንደአስፈላጊነቱ ሊለዋወጥይችላል፡፡

## ፴፭ <u>የኮሚቴ ስብሰባ</u>

፩ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለስራው ባስፈለገ መጠን በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ሰብሳቢውና ሌሎች ሶስት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫ የኮሚቴው ውሳኔ የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ያቀረበው ሃሳብ ያልፋል፡፡ በሀሳብ የተለየው አካል የተለየበትን ምክንያ በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡

## ፴፮ <u>ከአባልነት ስለመሰረዝና ከስብሰባ ስለመነሳት</u>

፩ ማንኛውም የኮሚቴ አባል ክስ ከቀረበበት ሰራተኛ ጋር ፀብ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ለዚያ ብቻ ከስብሰባው እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

፪ ማንኛውም የኮሚቴ አባል

ሀ) በኮሚቴው በመለየት ላይ ያለን ጉዳይ በሚመለከት ሚስጥር ያባከነ

ለ) የኮሚቴውን ስራ በማናቸውም አኳኋን ያደናቀፈ ፣ወይም

ሐ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 የተመለከቱትን መመዘኛዎች ያጓደለ እንደሆነ ከአባልነት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## ፴፯ <u>ቅሬታ የማቅረብ መብት</u>

፩ ማንኛውም መምህር፣ ርዕሰ መምህርና ሱፐርቫይዘር መብቴ ተጓድሎብኛል ወይም በደል ተፈጽሞብኛል በማለት ቅር የተሰኘ እንደሆነ ቅሬታውን እንዲታይለትና የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድለት ቅሬታውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የማቅረብ መብት አለው፡፡

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. ከህጎችና መመሪያዎች አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም

ለ. ከመብቶችና ጥቅሞች አጠባበቅ፣

ሐ. ከስራው አከባቢ ጤንነትና ደህንነት ሁኔታዎች፣

መ. ከስራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ፣

ሠ. ከስራ አፈጻጸም ምዘና

ረ. በስራ መደቡ የስራ ዝርዝር ሳይሸፈኑ እንዲፈጽሙ የሚሰጡ ተግባራት፣

ሰ. በአለቆች ከሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ ተጽዕኖዎች

ሸ. ከዲሲፒሊን እርምጃ አወሳሰድ ወይም

ቀ. የአገልግሎት ሁኔታዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ምክንያት በደል ደረሰብኝ የሚል ማንኛውም መምህር፣ ርዕሰ መምህርና ሱፐርቫይዘር ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፴፰ የቅሬታ ማመልከቻ**

፩ ቅሬታው እንዲሰማለት የሚፈልግ አካል የቅሬታ ማመልከቻውን ለመስሪያ ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፪ የቅሬታ ማመልከቻ የሚከተለውን መያዝ አለበት፤

ሀ. የአመልካች ስምና አድራሻ

ለ. የስራ መደቡ መጠሪያ

ሐ. የቅሬታ የቀረበበት ሰራተኛ /ኃላፊ ስም/

መ. የቅሬታው መንስኤ

ሠ. ደጋፊ ማስረጃዎች /ካሉ/

ረ. አመልካች የሚሻውን መፍትሄ

ሰ. ቀንና ፊርማ መኖር አለበት፡፡

፫ የቅሬታቸው መንስኤ አንድ አይነት የሆኑ አመልካቾች የቅሬታ ማመልከቻቸውን በተወካያቸው አማካይነት በቡድን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

**፴፱ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜና ገደብ**

፩ ቅር የተሰኘ ማንኛውም መምህር፣ ርዕሰ መምህርና ሱፐርቫይዘር ጉዳዩን ለቅርብ አለቃው ወይም ለሚመለከተው የስራ ኃላፊ በጽሁፍ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ አስር የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ለመስሪያ ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታውን ማመልከቻ ሊያቀርብ ያልቻለ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ፵ ቅሬታውን ስለማጣራት

፩የመስሪያ ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፴፰ በየተደነገገውን አሟልቶ የቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡

፪ ኮሚቴው፣

ሀ. የቅሬታ ማመልከቻውንና አግባብ ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመር፣

ለ. ከአመልካቹ እና ከአመልካቹ የቅርብ አለቃ ወይም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠው የስራ ኃላፊ ጋር በመወያየት እና

ሐ. አግባብ ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና የአሰራር ልምዶች በማገናዘብ፣ የቀረበለትን ቅሬታ ያጣራል፡፡

፫ ኮሚቴው የምርመራውን ውጤትና የውሳኔ ማመልከቻውን ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚመለከተው ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

# ክፍል ሰባት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፵፩ የማስረጃ ወጭ

የማስረጃዎች አቀራረብ የገንዘብ ወጭ የሚያስከትል ከሆነ ማስረጃው እንዲቀርብለት የሚፈልገው ወገን ለሚያቀርበው ማስረጃ የሚያስፈልገው ወጭ ራሱ ይችላል፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ማስረጃ ይሆኑኛል ያላቸው በከሳሹ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ተቋም ይዞታ ስር ከሆነና በዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲቀርብ ከታዘዙ የሚያስከትለው ወጪ እንዲሸፍን አይጠየቅም፡፡

## ፵፪ ተከሳሽ ተወካይ መወከል ስለመቻሉ

ተከሳሽ በዲሲፕሊን ወይም በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ላይ በሚከራከርበት ጊዜ የመረጠውን ሰው ይዞ ለመቅረብ፣ ለመወከል ወይም እንዲከራከርለት ለማድረግ መብት አለው፡፡ ይህንንም ተከሳሽ ኮሚቴው ፊት ቀርቦ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

## ፵፫ የተሻሩ መመሪያዎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፵፬ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም**

**ጀማሉ ጀንበር /ዶ/ር/**

**በምክትል ከንቲባ ማእረግ**

**የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ**